Seattle Parks & Recreation

# በቅርቡ ይመጣል!

## የደቡብ ፓርክ መጫወቻ ሜዳ (South Park Playfield) ማስያዝ ይፈልጋሉ?

ሜዳውን ለአንድ ጊዜ ወይም በመደበኛነት ለመሰልጠን ሊጠቀምበት የሚፈልግ የስፖርት ቡድን ወይም ዝግጅት አለዎት?

ከመጪው ጥር ወር ጀምሮ ሜዳው ለደቡብ ፓርክ (South Park) ማኅበረሰብ ክፍት የሚደረግ ሲሆን፣ አግባብነት ላላቸው ዝግጅቶች/የተጠቃሚ ቡድኖች ከክፍያ ነጻ ይሆናል!



# **የደቡብ ፓርክ መጫወቻ ሜዳን (South Park Playfield) ለመጠቀም እንዴት ቦታ ማስያዝ ይቻላል?**

1. **በኦንላይን ማመልከቻ ያስገቡ።** የደቡብ ፓርክ መጫወቻ ሜዳ (South Park Playfield) መደበኛ የሥራ ጊዜ ከሰኞ-ዐርብ ከ5፡30 ፒ.ኤም በኋላ ሲሆን፣ ቅዳሜ እና እሁድ ደግሞ ከ9 ኤ.ኤም - 10 ፒ.ኤም ነው።

2. **ሜዳውን መጠቀም መቻልዎን ያረጋግጡ።** ማመልከቻዎ እንደደረሰን የአትሌቲክስ መርሀ-ግብር ጽሕፈት ቤታችን (Athletic Scheduling Office) ሜዳውን መጠቀም የሚያስችሉዎን መስፈርቶች እንዳሟሉ ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁዎታል፡-
   - ከደቡብ ፓርክ (South Park) ጋር ያለዎት ግንኙነት ምንድን ነው?
   - ደቡብ ፓርክ (South Park) ውስጥ ከማሰልጠን ወይም የማኅበረሰብ ዝግጅቶች ላይ ከመሳተፍ አኳያ ያለዎት ልምድ/ታሪክ ምን ይመስላል?
   - የሚያዘጋጁት ዝግጅት ለ ደቡብ ፓርክ (South Park) አዲስ የሆነ ወይም ገና እያደገ ያለ ስፖርት/እንቅስቃሴ ነው?
   - ከዝግጅቱ ተሳታፊዎች ውስጥ ቢያንስ ከ65% በላይ የሚሆኑት ከደቡብ ፓርክ (South Park) (98108 እና 98106) እና አካባቢዎቹ የመጡ ግለሰቦች እንደሆኑ የሚያሳይ የስም ዝርዝር ሊያቀርቡ ይችላሉ?

3. **ፈቃድዎን ያግኙ።** ሜዳውን ለመጠቀም የተፈቀደላቸው ቡድኖች ቀኑን እና ሰዓቱን ጨምሮ መርሀ-ግብር የተያዘለትን የሜዳ ጊዜ የሚያረጋግጥ ፈቃድ ይደርሳቸዋል።

## **ማሳሰቢያዎች፡-**

- ሜዳው ተደራሽ የሚሆነው በደቡብ ፓርክ (South Park) እና አካባቢዎቹ ለሚኖሩ ማኅበረሰቦች ወይም ለደቡብ ፓርክ (South Park) ማኅበረሰብ ነጻ ፕሮግራሞች ለሚያቀርቡ ተጠቃሚዎች/የተጠቃሚ ቡድኖች ብቻ ነው።
- የሙከራ ፕሮግራሙ እየተካሄደ ባለበት ጊዜ ሜዳው ከክፍያ ነጻ ነው።
- በሜዳው ላይ የሚካሄድ ዝግጅት በሌሉባቸው ጊዜያት ከክፍያ ነጻ ያለ ቀጠሮ መጥቶ መጠቀም እና መጫወት ይቻላል።
- በሙከራ ፕሮግራሙ እና በቦታ ማስያዣ መርሀ-ግብሩ ወቅታዊ ዝርዝር ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ በPR South Park ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል።

*ይህ የሙከራ ፕሮግራም እየተካሄደ ባለበት ወቅት ከዚህ ቀደም ሜዳውን ለተጠቀሙ ቡድኖች የተለየ መስተንግዶ አይደረግም፣ ሁሉም ሰው የሙከራ ፕሮግራሙን ደንብ መከተል ይኖርበታል።

ጥያቄዎች አሉዎት? ኤሜይል ለathleticfieldscheduling@seattle.gov ይላኩ